# የቫንኮቨር ኢትዮጲያውያን ያፈሩት ሀብትና ንብረት ለወያኔ እጅ መንሻ አይሆንም።

ኢትዮጵያውያን የቫንኮቨርን ምድር በስደተኝነት ከረገጡ አርባ ዘመን አስቆጥረዋል። በዚህ አጭር የማይባል የስደት ወቅት እግራቸው በረገጠው ምድር ላይ ሁሉ የኢትዮጵያዊነት አሻራ እየተዉ ማለፍ ግድ ነውና ባሕላቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ልምዳቸውን ለሌላው እያስተዋወቁ፡ እነሱም የሌላውን ከራሳቸው ጋር እየቀላቀሉ ለተተኪ አዲስ ስደተኛ እያወራረሱ አዲስ መጪውም የራሱን እየጨመረበት ሲጓዝ ወደ ግማሽ ምዕተ ዓመት እየተጠጋ ነው። በዚህ የስደት ሕይወት ኢትዮጵያዊው የገነባውን የሚያፈርስ፣ የተሰበሰበውን የሚበትን አብሮ በቀል ጸረ ኢትዮጵያዊው ወያኔም በስደተኛነት ጋር ተሰይሟል።

ኢትዮጵውያን ስደት ሲወጡ የሚተማመኑበት ቢኖር አምላካቸውንና ስንቃቸውን ብቻ ነው። መጸሐፍ ቅዱስ፤ ውዳሴ ማርያም እና ቅዱስ ቁርዐን የስደተኞች ዋናው መሳሪያም መመሪያም ናቸው። አንድ ወቅት በሞዛምቢኩ ሊምፖፖ ወንዝ ተወስደው አስከሬናቸው ተገኘ 7/ሰባት ሴቶች ማንነት የተለየው ከቦርሳቸው ውሰጥ በተገኘ ውዳሴ ማርያም ነበር። ብዙዎች ወድቀው ቀርተዋል። በእሳት ተቃጠሉ፤ በበረሀ ወባ የተጠቁ፤ በእባብ ተነድፈው፤ በዘንዶ ተውጠው፤ በአውሬ ተበልተው፤ በባህር ሰምጠው… ወ.ዘ.ተ ወገኖቻችን ቁጥር እጅግ ብዙ ነው።

ለስደቱ መነሻ ቀደም ሲል ለ17 ዓመት ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አሁን ለ22 ዓመታት ዘረኛው የሕወሓት/ወያኔ አገዛዝ ነው። ለዚህ ደግሞ ከበቂ በላይ ማስረጃ ስላለ ያንባቢን ጊዜ ለማባከን አልፈልግም። የሩቁን ትተን የቅርቡ እንኳን ጋምቤላን ለሕንድ፡ ዓረብና ለቻይና ሲቸበችብ በመሬቱ ላይ የነበረው ሕዝብ የት ገባ? ቤቱ እላዩ ላይ በግሬደር እየፈረሰበት መሬቱን ለሱዳን ሲሰጥ ሕዘቡንም ወደ ሱዳን ወህኒ ቤት የተጣለው፤ አማራ ነህ ቤት ንብረቱ፤ ድርጅቱ በሕወሓት የቀድሞ ተዋጊዎች እየተነጠቀ የተባረረው የት ገባ? የቻለ ይሰደዳል ያልቻል እዚያው አዲስ የመከራ ሕይወት ይጀመራል። በረሀብም የሚያለቀውን ቤት ይቁጠረው። ባጠቃላይ ወየኔ የግፍ መፈልፈያ ነው።

ሕወሓት/ወያኔ ይህ ግፍ አልበቃ ብሎት ለነፍሳቸው ሸሽተው የተሰደዱትን እየተከታተለ በየስደት ካምፑ የገደላቸው፤ በየባዕድ አገሩ ማጅራት መቺዎችን እየገዛ ያስፈጃቸው ወገኖች ቀላል አይደለም:: ከዚህ ሁሉ የከፋ መከራ አልፈው የስደት መዳረሻ በሆኑ አገሮች "ሀ" ብለው ኑሮን ሲጀምሩ እዚህ ላደረሳቸው አምላክ የሚያመሰግኑበት ቤተ ክርስቲያን፤ ለችግራቸው የሚረዳዱበት ማሕበር፤ ዕድር/ዕቁብ ሲጀመር ወያኔም እንደ "H.I.V" ኤድስ ቫይረስ ሴሎችን ተመሳስሎ ግበቶ ሕይወትን አደጋ ላይ እንደሚጥል ሁሉ የእኛኑ ጓደኞች በዘርና በጥቅም እየገዛ በቤተ ክርስቲያንና ማናቸውንም መሰባሰቢያ ማዕከሎች

እያፈራረሰ ሕዝቡን በዘር በሃይማኖት እየከፋፈለ ያበጣብጣል። በመላው ዓለም በኢትዮጵያውያን ስደተኞች የተቋቋሙ ዐብያተ ክርስቲያን የዘረኛው ወያኔ የብተና አደጋ ያላጋጠማቸው የሉም። ብዙዎቹ በፍርድ መብታቸውን አስከበረዋል። አሁንም ቢሆን ወያኔ በራሱ ሕገወጥ ሲኖዶስ ስር ለማድረግ እየጣረ ነው።

የቫንኩቨር ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በዘር ሀረግና ራሳቸውን ለወያኔ የሸጡ ርካሽ ባንዳዎች በመታገዝ ሁሉም በጋራ የሚያመልክበትን ቤተ ክርስቲያን ከፍለው ገንዘቡን ዘርፈው ተገነጠሉ። እንደገናም ቤተ ክርስቲያኗ ከዚያ ሁሉ የመከፋፈል አደጋ አንሰራርታ እርምጃዋ እያማረ ሲሄድ አሁንም ከሕ-ገወጡ የወያኔው ሲኖዶስ ያልተላቀቀ ካህንና አንድ በነፃ አገልግሎት ስም ገብቶ እስከ ሂሳብ ሹምነት የደረሰ ግለሰብ $18000/አስራስምንት ሺህ የካናዳ ዶላር ወስዶ ምዕመናኑን አሳስቶ ሁለተኛውን ግንጠላ አካሂያዱ። በዚህ ብቻ አላቆመም ለየት ያለ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት በሕጋዊው ሲኖዶስ ስር እንደሆኑ በማስመሰል ምዕመኑን፡ የሲያትል አባቶችን እንዲሁም ያካባቢውን ሕዝብ ሲያሳስት ቆይቶ ወያኔያዊ ተልዕኮው ሲያጠናቅቅ የወያኔ ቀንደኛ ግብረበላ መሆኑን አስመስክሯል።

ሰሞኑን በዕብሪት ተነሳስተው ለዐባይ ግድብ ቦንድ እንሸጣለን በማለት በአክሱም ኢትዮጲያውያን ምግብ ቤት ዝግጅት ላይ የማንን ምንነት ያጋለጠ ከመሆኑም በላይ እነዚህን የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች ተከትለው የተሳሳቱ ስህተታቸውን፤ የሚያርሙበት መንገዳቸውን የሚያስተካክሉበት፤ በዚህ ጉዳይ ከተጣሉት ወንድሞቻቸው ይቅር የሚባባሉበትና በአጠቃላይ ቆም ብለው እራሳቸውንም የሚመረምሩበት ወቅት መሆኑን ጠቋሚ ወቅት ነው።

ለመሆኑ በከተማችን የሚገኘው አክሱም ምግብ ቤት ማን፤ የማን፤ ለምንስ ተግባር የተቋቋመ ነው? በሎ መጠየቅ የግድ አስፈላጊ በመሆኑ ለአንባቢያን ትንሽ ግንዛቤ ማስጨበጥ እፈልጋለሁ። ምግብ ቤቱ ከመከፈቱ በፊት ባለቤቱ በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ውስጥ በመመረጥ በወቅቱ የነበሩትን አመራር በጥቅም በመደለል ተገንጣይ ወያኔን ደግፈው እንዲቆሙ አስደረገ፤ የሚሊኒየሙ በዐል ሁለት በመክፈል በወቅቱ ነበረውን አመራር ችግር ውስጥ ከትቶ እስካሁን ድረስ ወንድማማቾች በጠላትነት እንዲተያዩ ያደረገ ነው። በሕጻናት ስፖርት ክበብ፤ በቤተ ክርስቲያን መከፈል የተጫወተው ሚና፤ ቤተ ክርስቲኗ ስትከፈል ኮሚኒቲው የወያኔን ጎራ ደግፎ እንዲቆም የአስደረገ መሆኑን ሁሉም የሚያውቀው እውነት ነው።

ሉሲ እና ድንቅነሽ ግሮሰሪና ምግብ ቤት አንድ ጊዜ ሲከፈት ገንዘቡ ከየት መጣ? ምንስ ተግባር ሊያከናውን ነው? እውን እነኝህ የንግድ ድርጅት አትራፊና ለትርፍስ የተቋቋመ ነው? ነገሩ እንዲህ ነው; ንግዱም ሆነ ትርፉ በእኛ ሕይወትና ነፃነት፤ በወገኖቻችን ደምና ሰቆቃ፤ በሀገራችን ሀበት ንብረት ቅርሳ ቅርስ እዘረፉ ወደ ውጭ ማሸሽ ስራ ነው። ለH.I.V መከላከያ፤ ለሕጻናት መርጃ፡ ለትምህርት ማስፋፊያ ከበጎ አድራጊዎች የሚለገሰውን ገንዘብና ቁሳቁስ አገር ውስጥ እየተቸበቸበ ንብረቱን በውጭ ባንክ ለማስቀመጥና ድርጅት ለመገዛት በተጓዳኝም የሕወሓትን ስለላና የሀሰት ፕሮፖጋንዳ ማሰራጫ መሆኑ ግልጽ ነው። ቦንድ እሸጣለሁ ብሎ 4/አራት ሴኩሪቲ ከውጭ አንድ ከውስጥ በር ላይ አቁሞ መጠጥና

ምግብ በነፃ እያደሉ በ14 ተጋባዥ እንግዶች የሚገኘው የትርፍ ስሌት እንተወውና ይኸው ከሕወሓት የዘር ሀረግ የተገኘው ነጋዴ አንዱ ወንድሙ የወየኔ ዳኛ ሌላዋ እሁቱ ደህንነት የሆኑ “አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ “ ሆኖ እየተነገደብን መሆኑ ነው።

ከላይ አጠር ባለ መልኩ ለመገለጽ የተሞከረው ከተሰሩብን ደባዎች በጣም ጥቂቱ ነው። ይህንን ያልተረዳ በቫንኮቨር ያለ ኢትዮጵያዊ አለ ማለት አይቻልም። ካለ አንድም በዘር ወይም በብር አለያም በይሉኝታ የታሰረ መሆን አለበት። ይሉኝታም ቢሆን አገር እስከፈርስ መጠበቁ ሚዛናዊ አይደለም። እውነቱ እንደበጋው ፀሐይ ፍንትው ብሎ እየታየ በሕገ ወጡ የወያኔ ሲኖዶስ የሚገለገሉ ወያኔ ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን በፀረ ኢትዮጵያዊነት ጎራ መቆማቸውን፤ የእውነትን አምላክ ማስቀየማቸውን፡ አገር እንድትበታተን ማገዛቸውን ይዘነጉታል? ለማን ይድላው ተብሎ ከሀገር ገንጣይ ጎን ይቆማል? ዛሬም ይሁን ነገ የራሳችሁ ሕሊና በራሳችሁ ላይ እስኪፈርድ ሳትዘገዩ ተመለሱ። አስራስምንት ሺህ የወሰደው ግለሰብም ወያኔነቱ ከታወቀ ለምን በሕግ አይጠየቅም? ከምዕመናን የተሰብስብ ገንዘብ ቦንድ ተራ ሲለከሰከስ ዝም ተብሎ መታየት ስለማይገባ ሕጋዊ እርምጃ ባስቸኳይ ያሻል እያልኩ ስሰናበታችሁ በቸር እንደምንገናኝ በመተማመን ነው።

ተዋናይ